በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ 213623

ሚያዚያ 25 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነአ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች፡- ጉምሩክ ኮሚሽን ሞጆ ቅ/ጽ/ቤት - ነ/ፈ ጋዲሳ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ደብል ኤስ ቢዝነስ ኃ/የተ/የግ/ማህበር- አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የተያዘው ክርክር የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜን የሚመለከት ሲሆን የሰበር አቤቱታው የቀረበው አመልካች በቀን 27/12/2013 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 202933 በቀን 20/11/2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልኝ በማለት ስለጠየቀ ነው።

ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው የጉምሩክ ጉዳዩች አቤቱታ አጣሪ ጽ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም የአሁን ተጠሪ ይግባኝ ለታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ያቀረበ ሲሆን ኮሚሽኑም ክርክሩን መርምሮ ተጠሪ ላስገባው እቃ ዋጋ አተማመን ዘዴ በአዋጁ በአንቀጽ 91(2) መሰረት መስተካከያ መደረግ ያለበት መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት ተጠሪ አስቀድሞ ያቀረበው የግብይት ዋጋ ተቀባይነት የለውም ቢባል እንኳን በአመልካች የተሰጠውን ዋጋና ተጠሪ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የግብይት ዋጋ በማለት ያቀረበው ዋጋ አማካኝ ዋጋ በመውሰድ ዋጋውን መወሰን ከህግም ከፍትሐዊነትም አንጻር አግባብነት ያለው ሁኖ ኮሚሽኑ አግኝቶታል በማለት ተጠሪ ያስገባው ዕቃ ዋጋ በአንድ አይነት ዕቃ ዋጋ አተማመን ዘዴ ዩ.ኤስ.ዲ 3.05 እንዲሆን በማለት ወስኗል፡፡ ውሳኔውም በኮሚሽኑ አባላት በቀን 22/09/2011 ዓ.ም መፈረሙ በውሳኔው ተመልክቷል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በቀን 07/01/2012 ዓ.ም የተፃፈ የይግባኝ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ የአሁን አመልካች ለይግባኙ መልስ እንዲያቀርብ ታዞ ባቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 155(3) መሰረት ይግባኙ መቅረብ ያለበት ውሳኔ በተሰጠ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ በመሆኑና ይግባኙ የቀረበው ውሳኔ ከተሰጠ ከ 3 ወር ከ 20 ቀናት በኃላ በመሆኑ ወደፍሬ ጉዳዩ መግባት ሳያስፈልግ መዝገቡ ተዘግቶ ልሰናበት በማለት ተከራክሯል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን አባላት ውሳኔው በአንድ አባል ከተሰራ በኃላ በተለያ ጊዜ የሚፈርሙበት በመሆኑ ውሳኔ በተሰጠ በ 30 ቀን ውስጥ ቅሬታ ለፍርድ ቤት ማቅረብ ላይ ችግር በመፈጠሩ ህጉ ተሻሽሎ የጉባኤው የጽሁፍ ውሳኔ በደረሰው በ 30 ቀን ውስጥ ቅሬታ ማቅረብ እንደሚቻል ተደንግጓል፤ በጉባኤው የተሰጠው ውሳኔ በፅሁፍ የደረሰኝ ነሐሴ 15/2011 ዓ.ም ሆኖ የይግባኝ ቅሬታው ለከፍተኛው ፍርድ ቤት የቀረበው በህጉ የተመለከተው የጊዜ ገደብ ሳያልፍ መስከረም 7/2012 ዓ.ም በመሆኑ መቃወሚያው ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡

የከፍተኛው ፍርድ ቤት ክርክራቸውን መርምሮ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/96 አንቀጽ 155(3) መሰረት በኮሚሽኑ ውሳኔ ላይ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ቅር የተሰኘ ማንኛውም ወገን ውሳኔ በተሰጠ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ይግባኙን ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ማቅረብ እንደሚችል የተደነገገ ሲሆን በዚህ የህግ ድንጋጌ መሰረት ተጠሪ የይግባኝ አቤቱታውን ባለማቅረቡ በይርጋ የታገደ ነው፤ ተጠሪ በህጉ በተደረገ ማሻሻያ መሰረት የጉባኤው የፅሁፍ ውሳኔ በደረሰው በ30 ቀን ውስጥ ቅሬታውን ማቅረብ እንደሚችል ያቀረበውን ክርክር በተመለከተ ጉዳዩ የጉምሩክ አዋጅን የሚመለከት በመሆኑ ፍርድ ቤቱ አልተቀበለውም በማለት ወስኗል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱም ክርክሩን መርምሮ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በሰጠው ውሳኔ የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

983/2008 አንቀጽ 57(1) በታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ወገን ውሳኔው በደረሰው በ 30 ቀናት ውስጥ ይግባኙን ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ሊያቀርብ እንደሚችል ተደንግጓል፤ ክርክር ተነሳበት ጉዳይ ተጠሪ ከውጪ ያስገባቸውን ዕቃዎች ዋጋ አተማመን የሚመለከት የጉምሩክ ጉዳይ ቢሆንም የታክስ አስተዳደር አዋጁ የጉምሩክና ሁሉንም የግብር ጉዳዮች ለማስተዳደር የወጣ በመሆኑ ለተያዘውም ጉዳይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፤ የኮሚሽኑ አሰራርም ባለጉዳዮቹ በተገኙበት ውሳኔ የሚሰጥበትና ውሳኔ በተሰጠበት ቀን ለባለጉዳዮቹ ማድረስ የሚቻልበት ባለመሆኑ የታክስ አስተዳደር አዋጁ የያዘው አቋም የኮሚሽኑን አሰራር ያገናዘበ መሆኑን መገንዘብ ተችሏል፤ ተጠሪም ውሳኔው ከደረሰው ጀምሮ የይግባኝ ጊዜው ሳያልፍ በ30 ቀን ውስጥ ይግባኙን ያቀረበ በመሆኑ ከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ በአግባብ ሆኖ አልተገኘም በማለው ውሳኔውን ሽሮ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ወደ ይግባኙ ፍሬ ነገር በመግባት ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥ በማለት ጉዳዩን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 341(1) መሰረት መልሷል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘታቸው ነው። አመልካች በቀን 27/12/2013 ዓ/ም ባቀረበው ቅሬታ ጠቅላይ ፍ/ቤት ከክርክሩ ጋር አግባብነት የሌለውን አዋጅ ቁጥር 983/2008 በመጥቀስ የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፤ የጠቅላይ ፍ/ቤት ውሳኔ የፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 325 ድንጋጌ እና የጉምሩክ አዋጅ 859/2006 አንቀጽ 155(3) ድንጋጌ የጣሰ ነው፤ የተጠሪ ይግባኝ አቤቱታ ይግባኝ ማቅረቢያ ግዜው ያለፈበት በመሆኑና በማስፈቀጃ ቅሬታውን ማቅረብ እየቻለ ይህን ሳያደርግ በህግ ድጋፍ የሌለው ክርክር ማቅረቡ አግባብ ስላልሆነ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ እንዲሻርና የከፍተኛው ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲጸና በማለት ጠይቋል፡፡

ቅሬታው በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ ለክርክር መነሻ የሆነው የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ አወሳሰን በተመለከተ የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አግባብነት ያለው ስለመሆኑ ለማጣራት በሚል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብና ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

ተጠሪ በቀን 01/04/2014 ዓ.ም ባቀረበው መልስ ከታክስ ጋር ተያይዘው በታክስ ይግባኝ ኮሚሽን የሚሰጡ ውሳኔዎች በሙሉ የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜን አስመልክቶ እየታዩ ያሉት በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/08 እንጂ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አይደለም፡፡ በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/08 አንቀጽ 57(1) መሰረት በኮሚሽኑ ውሳኔ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ቅር የተሰኘ ታክስ ከፋይ ውሳኔው በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ይግባኝ ቅሬታውን ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሊያቀርብ እንደሚችል በተደነገገው መሰረት ተጠሪ የኮሚሽኑን ውሳኔ በ15/12/2011 እንደወሰደ በ30 ቀናት ውስጥ ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ መሆኑ ተረጋግጦ የተሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍበት የህግ ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም የአመልካች አቤቱታ ውድቅ እንዲደረግና የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ውሳኔ እንዲጸና በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካችም ክርክሩን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከፍ ሲል በአጭሩ የገለጽነው የጉዳዩን አመጣጥ ነው፡፡ በበኩላችን ለሰበር ችሎቱ የተያዘውን ጭብጥ ከግራቀኙ ክርክር እና ከህጉ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው አመልካች አጥብቆ የሚከራከረው የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 ለተያዘው ጉዳይ ተፈጻሚነት የለውም፤ ይልቁንም ጉዳዩ ከፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 325 እና ከጉምሩክ አዋጅ 859/2006 አንቀጽ 155(3) ድንጋጌ አንፃር ታይቶ የተጠሪ ክርክር ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ነው፡፡ ተጠሪ በበኩሉ በአዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 57(1) መሰረት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ሊታይ እንደሚገባ ተከራክሯል፡፡

እንደሚታወቀው የፌዴራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 እንዲወጣ ከተፈለገባት ዓላማ አንዱ ታክስ ከፋዮች በታክስ ውሳኔ ረገድ የሚኖራቸውን ቅሬታ ማቅረብ የሚችሉበት ተደራሽነት ያለው፣ በሚገባ የተደራጀ እና የተቀላጠፈ ውሳኔ መስጠት የሚያስችል ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ መገኘቱ ስለመሆኑ በአዋጁ መግቢያ (Preamble) ላይ ተመልክቷል፡፡ ይህን የአዋጁን አላማ ተግባራዊ ማድረግ ይረዳ ዘንድ የአዋጁ ምዕራፍ ዘጠኝ የሚፈጠር አለመግባባት አቤቱታ የሚቀርብበትን ስርዓት ደንግጓል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ስር የሚገኘው አንቀጽ 57(1) በታክስ ይግባኝ ኮሚሽን በነበረ ክርክር ተካፋይ የነበረ ሰው ኮሚሽኑ በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ እንደሆነ የኮሚሽኑ ውሳኔ ማስታወቂያ በደረሰው በ30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ሊያቀርብ እንደሚችል ተደንግጓል፡፡

ከድንጋጌው መገንዘብ እንደሚቻለው በታክስ ይግባኝ ኮሚሽን በነበረ ክርክር ተካፋይ የነበረ ሰው ኮሚሽኑ በሰጠው ውሳኔ ይግባኝ ሊያቀርብ የሚችልበት ጊዜ የሚታሰበው የኮሚሽኑ ውሳኔ ማስታወቂያ ከደረሰው ጊዜ ጀምሮ ከሚሆን በቀር ኮሚሽኑ ውሳኔ ከሰጠበት ቀን ጀምሮ አይደለም፡፡

*ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

በሌላ በኩል አመልካች አዋጅ ቁጥር 983/2008 የጉምሩክ ህግን ወይም ከጉምሩክ ጉዳዮች ጋር ተያይዘው የመጡ ክርክሮችን የሚመለከት አለመሆኑን በማንሳት ተከራክሯል፡፡ ይሁንና በአዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 2(4) ስር በግልጽ እንደተመለከተው "ባለስልጣን" ማለት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣንን፣ እንዲሁም የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ገቢዎች ቢሮን የሚመለከት ነው፡፡ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣንን ጨምሮ እነዚህ ባለስልጣኖች በሚሰጡት ውሳኔ ላይ ደግሞ ይግባኝ የሚቀርበው በአዋጁ ከአንቀጽ 52 ጀምሮ በተደነገጉት ድንጋጌዎች በተዘረጋው ሥርዓት መሰረት ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች አዋጅ ቁጥር 983/2008 የጉምሩክ ህግን ወይም ከጉምሩክ ጉዳዮች ጋር ተያይዘው የመጡ ክርክሮችን እንደማይመለከት እንዲሁም አዋጁ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የሚያሳልፈውን ውሳኔ ተከትሎ የሚቀርብ ይግባኝን እንደማይመለከት በማንሳት ያቀረበው መከራከሪያ ተቀባይነት የለውም፡፡

በአጠቃላይ አመልካች አዋጅ ቁጥር 983/2008 የጉምሩክ ህግን ወይም ከጉምሩክ ጉዳዮች ጋር ተያይዘው የመጡ ክርክሮችን የሚመለከት አይደለም በማለት የሚያቀርበው ክርክር የታክስ አስተዳደር አዋጁ የተደነገገበትን አላማ እንዲሁም የአዋጁን ይዘትና መንፈስ መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡ ተጠሪ የኮሚሽኑ ውሳኔ ማስታወቂያ ከደረሰው ጀምሮ በህግ በተፈቀደው ጊዜ ውስጥ ይግባኝ ያቀረበ መሆኑ ተረጋግጦ በጠቅላይ ፍርድ ቤቱ የተሰጠው ውሳኔ ህጉን የተከተለ ነው ከሚባል በቀር የሚነቀፍ ባለመሆኑም ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 202933 በቀን 20/11/2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

2. በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 243644 የተጀመረው ክርክር ታግዶ እንዲቆይ በዚህ መዝገብ በአጣሪ ችሎቱ ጥቅምት 8/2013 ዓ.መ የተሰጠው ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

3. በሰበር ስለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

አ/ኃ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም